የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 31.
ADDIS ABABA 22nd May, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፭/፪ሺህ ዓ.ም

የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፹፱

CONTENTS

Proclamation No. 575/2008

Ethiopian Wildlife Development and Conservation Authority Establishment Proclamation Page 4089

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፭/፪ሺህ

## የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ዓይነት የተፈጥሮ ውበት ያላቸው ብርቅዬ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ባለቤት በመሆኗና ይህም ሀብቷ በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ ሚና ያለው ሆኖ ለቱሪዝም፣ ለትምህርትና ለሳይንስ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ፣

ይህ ሀብት በተገቢው መንገድ እንዲጠበቅና እንዲለማ በማድረግ ቀጣይነት ያለው ጥቅም ለመስጠት እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መንግሥት በአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት ላይ እተባባሰ የመጣውን የእልቂት አደጋ ለመግታትና ከሀብቱ አገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች እንድታገኝ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና አሁን ካለው ዓለም አቀፍ የዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ ልማትና አጠቃቀም አኳያ ንዑስ ዘርፉን ማጠናከር በማስፈለጉ፣

በአገሪቱ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ትኩረት ሰጥቶ ለመንቀሳቀስና ከመስኩ የሚገኘውን ጥቅም ለማጎልበት በፌዴራል ደረጃ ይህን የሚያስፈጽም አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 575/2008.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN WILDLIFE DEVELOPMENT AND CONSERVATION AUTHORITY

**WHEREAS,** Ethiopia possesses diverse, rare and endemic species of wildlife which are of great value to tourism, education and science;

**WHEREAS,** it is necessary to undertake appropriate conservation and development of wildlife for its sustainable use;

**WHEREAS,** by halting the ever growing wildlife threatening conditions and enable the country to obtain economic and social benefits from its wildlife resource, it has become necessary to strengthen the sub-sector in accordance with the current global development utilization and conservation standard;

**WHEREAS,** to provide proper attention for the development, conservation and utilization of the country's wildlife resource and maximize its benefit, it has become necessary to establish a government body at the federal level;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለ ሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፭/፪ሺህ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "የዱር እንስሳት አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፩/፲፱፻፺፱ ነው፣

፪/ "የዱር እንስሳት"፣ "የዱር እንስሳት ሀብት"፣ "የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ" እና "የዱር እንስሳት ውጤት" በዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ ፪ ሥር የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፣

፫/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።

## ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን /ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ/ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ጽሕፈት ቤቶች በሌሎች ሥፍራዎች ይኖሩታል።

## ፭. ዓላማ

የባለሥልጣኑ ዓላማ የአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ይሆናል።



## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Wildlife Development and Conservation Authority Establishment Proclamation No. 575/2008".

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ "Wildlife Proclamation" means the Development, Conservation and Utilization of Wildlife Proclamation No.541/2007;

2/ "Wildlife", "Wildlife Resource", "Wildlife Conservation Area" and "Wildlife Product" shall have the meanings assigned to them under Article 2 of the Wildlife Proclamation;

3/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Culture and Tourism, respectively.

## 3. Establishment

1/ The Ethiopian Wildlife Development and Conservation Authority (hereinafter referred to as the "Authority") is hereby established as an autonomous public agency of the federal government.

2/ The Authority shall be accountable to the Ministry.

## 4. Head Office

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may have wildlife conservation area offices elsewhere, as may be necessary.

## 5. Objectives

The objectives of the Authority shall be to ensure the development, conservation, and sustainable utilization of the country's wildlife resource.

## ፮. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ የዱር እንስሳት ሀብት ልማትን፣ ጥበቃንና አጠቃቀምን በተመለከተ የፖሊሲና የሕግ ረቂቅ እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀዱም በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

፪/ በሥሩ የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ይከላከላል፣

፫/ በውጭ ቱሪስቶች ለሚካሄድ አደን ፈቃድ ይሰጣል፣

፬/ ሆቴል፣ ካምፕ፣ ሎጅና ሌሎች አገልግሎቶች በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ እንዲቋቋሙ ፈቃድ ይሰጣል፣

፭/ ማናቸውንም የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድና የጤና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

፮/ የዱር እንሰሳት ውጤት በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ ለተመለከተው ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ውጤቱንም ይለካል፣

፯/ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት እንዲመዘገቡ ለማስቻል ዓለም አቀፋዊ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ እነዚህኑ መስፈርቶች ጠብቀው መተዳደራቸውን ይከታተላል፣

፰/ ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ ዕርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ ወገኖች ጋር ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመሰርታል፣

፱/ የዱር እንስሳት ሀብትን አስመልክቶ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣ ለሚመለከታቸው ዓለም ዓቀፍ ተቋማትም በየጊዜው ሪፖርት እያዘጋጀ ያስተላልፋል።

## 6. <u>Powers and Duties</u>

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ prepare and submit to the Ministry draft policies and laws relating to the development, conservation and utilization of wildlife resources; and follow up the implementation of the same upon approval by the government;

2/ develop and administer wildlife conservation areas established under it and control illegal activities committed in the areas;

3/ issue hunting permits to foreign tourists;

4/ issue permits for the establishment of hotels, campsites, lodges and other services in wildlife conservation areas;

5/ issue permits and health certificates to export and import any wildlife or wildlife products;

6/ control the utilization of wildlife products to ensure its compliance with the objectives of the permit, and make impact assessments on the product;

7/ ensure that wildlife conservation areas are established in accordance with international standards with a view to facilitating their registration by the World Conservation Union, and follow up their administration accordingly;

8/ establish international relations with all bodies having the potential of providing technical and other assistance for wildlife conservation;

9/ ensure the implementation of treaties to which Ethiopia is a party; compile and submit periodical reports to the concerned international institutions;

፲/ የዱር እንስሳትን በተመለከተ በማናቸውም ዓለም አቀፍ ስብሰባ ወይም ጉባዔ መንግሥትን ይወክላል፣

፲፩/ የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ጥናትና የሥልጠና ፕሮግራም ያካሂዳል፣ ወቅታዊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀነባብራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣

፲፪/ ለክልሎች በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ረገድ አስፈላጊውን እገዛ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣንና ተግባሩን ለሌሎች የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት በውክልና ይሰጣል፣

፲፫/ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፬/ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በተገባ የኮንሴሽን ውል መሠረት በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ይቆጣጠራል፣

፲፭/ በመንግሥት በጸደቀ ተመን መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፣

፲፮/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፲፯/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ፯. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፣

፩/ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፪/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

## ፰. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።



10/ represent the government in any international meetings and conferences relating to wildlife;

11/ conduct research and training programs and collect, process and provide to users up-to-date information on the conservation, development and utilization of wildlife;

12/ provide support to regions with respect to the development and conservation of wildlife, and delegate its powers and duties to other federal and regional government organs where necessary;

13/ prevent and control incidents of wildlife diseases within or outside of conservation areas;

14/ supervise wildlife conservation areas administered by private investors in accordance with concession agreements entered into with the federal government ;

15/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate approved by the government;

16/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

17/ carry out such other activities as are necessary for the fulfillment of its objectives.

## 7. <u>Organization of the Authority</u>

The Authority shall have:

1/ a Director General to be appointed by the Government upon the recommendation of the Minister; and

2/ the necessary staff.

## 8. <u>Powers and Duties of the Director General</u>

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority and shall, subject to the general directives of the Ministry, direct and administer the activities of the Authority.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃ ላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከተውን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ/ ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፣

ረ/ ስለባለሥልጣኑ የሥራ እንቅስቃሴ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ፱. በ ጀ ት

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## ፲. የሂሣብ መዛግብት

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል።

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ፲፩. የተሻሻሉና የተሻሩ ህጎች

፩/ የዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፲፯/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፲፯/ ተተክቷል፣

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a/ exercise the powers and duties of the Authority specified in Article 6 of this Proclamation;

b/ employ and administer employees of the Authority in accordance with the Federal Civil Service Laws;

c/ prepare the annual work programme and budget of the Authority and implement the same upon approval;

d/ effect expenditure in accordance with the approved budget and work programme of the Authority;

e/ represent the Authority in all its dealings with third parties;

f/ submit reports to the Ministry on the activities of the Authority.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Authority to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Authority.

## 9. Budget

The budget of the Authority shall be allocated by the Government.

## 10. Books of Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or by Auditors designated by the Authority.

## 11. Amendments and Repeal

1/ Sub-Article (17) of Article 2 of the Wildlife Proclamation is repealed and amended by the following new Sub-Article (17):

«፲፯/ ‘ባለሥልጣን’ ማለት የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፣»

፪/ በዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ውስጥ "ሚኒስቴሩ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር" በሚለው ተተክቷል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ ከተጠቀሱትን በስተቀር በዱር እንስሳት አዋጅ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "ሚኒስቴሩ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ባለሥልጣኑ" በሚለው ተተክቷል።

፬/ የዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ተሰርዞ አንቀጽ ፲፬፣ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰፣ ፲፱፣ እና ፳ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፲፫ ተሰርዞ አንቀጽ ፲፬፣ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰፣ እና ፲፱፣ ሆነዋል።

## ፲፪. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

የዱር እንስሳት የሥራ ዘርፍን የሚመለከቱ፡ የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል።

## ፲፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

"17/ ‘Authority’ means the Ethiopian Wildlife Conservation Authority;"

2/ The term "Ministry" under Sub-Article (2) of Article 4 and Sub-Article (2) of Article 17 of the Wildlife Proclamation is repealed and amended herein by the "Ministry of Culture and Tourism".

3/ Any reference to "Ministry" in the Wildlife Proclamation, other than those referred to in Sub-Articles (1) and (2) of this Article, are repealed and amended herein by the "Authority".

4/ Article 13 of the Wildlife Proclamation is repealed and Articles 14, 15, 16, 17, 18, 19 and 20 are re-numbered as Articles 13, 14, 15, 16, 17, 18 and 19, respectively.

## 12. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Ministry of Agriculture and Rural Development with respect to its activities relating to wildlife are hereby transferred to the Authority.

## 13. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of May, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**